# አሸባሪነት ሳይቀድም መቅደም

ጎሩይ ተወልደ

07/10/14

የዚህ ፅሁፍ መነሻ ፋክት መጽሄት በሰኔ 2006 እትሟ ይዛ የወጣችው አስገራሚው የተመስገን ደሣለኝ የሽብር ዘ ፍጥረት ፅሁፍ ነው፡፡ ታሪክን መናድ ባሻቸው መልኩ መሳልና ከገዥው መንግሥት ጋር እያቆራኙ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳቸውን መንዛት መደበኛ ሥራቸው ያደረጉት እየፃፉ በተመስገን ፎቶ የሚያወጡ ግለሰቦች አሁን ደግሞ በግላጭ እስላማዊ አክራሪነትን ወደ ሰማይ ሰቀለው መገፋትና በደል ያመጣው ሕዝባዊ አመፅ ነው እያሉን ነው፡፡ የፈረደባትን ኢትዮጵያ የአልሸባብና የአሸባሪነት ዓላማ ያደረጋት ኢሕአዴግ ነው እያሉን ነው፡፡

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በፓርላማ ስብሰባ ላይ አልሸባብን ለመዋጋት የኢትዮጵያ ጦር ሶማሊያ መግባት አለበት ብለው ሀሳብ ሲያቀርቡ በወቅቱ የነበሩት ተቃዋሚዎች ሲቃወሙና የኢዴፓው ልደቱ አያሌው ሲደግፉ መቼም መለስ ያቀረበው ሀሳብ ውድቅ አይደረግም፤ በውሣኔ ፀድቆ የኢትዮጵያ ሠራዊት አልሸባብን ለመዋጋት ሶማሊያ ገባ፤ የአሜሪካ ተልዕኮ አስፈፃሚና ቅጥረኛ ሆኖ ነው የገባው፤ ውጊያው ላይ አሜሪካኖች ሥምሪት ሲሰጡ በጄትም ሲያስደበድቡ ነበር የሚለው ተመስገን ስማቸውን የቀየራቸውን የሠራዊቱን አባላት እንዲህ አሉ፣ እንዲያ አሉ በማለት ይተርካል፡፡

ፅዮናዊነት በቴዎድሮስ ሔርዜል መጀመሩንና ወደ ቅድስቲቱ አገር በዓለም የተበታተኑ አይሁዶች ያደረጉትን ጉዞ፤ በአይሁድ ኮማንዶዎች የዚያን ጊዜዎቹ እሱ ባይጠቅሰውም እነ ይስሀቅ ራቢን አሪየል ሻሮን በዋናነትም እነ ዴቪድ ቤንጎሪያን የመሩትን ታላቁን የሐጋና ጦርነት ይጠቅሳል፡፡ በፈንጂ የማፈራረስ የአሸባሪነት እርምጃ በአይሁዶች መጀመሩን ተመስገን ይነግረናል፡፡

ወደ እኛም አገርና አጐራባቻችን ሶማሊያ ተመልሶ አልሸባብ (የወጣቱ ክንፍ) የበለጠ ለበቀል የተነሳው የኢትዮጵያ ሠራዊት በእስላማዊ ሕብረት ላይ በወሰደው

የከፋ እርምጃ መሆኑን፤ በኦብነግ የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃነት ግንባር ላይም የኢትዮጵያ ሠራዊት የወሰደው የከፋ እርምጃ ብዙ ዓለም አቀፍ ውግዘት እንዳስከተለበት ያስነብበናል፡፡ ይህ ግለሰብ በዚህ ፅሁፍ አልሸባብም ሆነ ኦብነግም በጭራሽ ሊነኩ አይገባም፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ድንበር አልፎ መግባት አልነበረበትም በማለት እስላማዊ አክሪሪ ኃይሎችን በሙሉ ጥብቅና ይከራከርላቸዋል፡፡ ይህ በአገራዊና ታሪካዊ ክህደት የተሞላው ቁማሩ ዋና ግብ በአገር ውስጥ አድፍጦ ያለውን እስላማዊ አክራሪ ኃይል በአጋርነት ወደ ራሱ የአመፅ አብዮት አጋርነት ማሰለፍ ነው፤ በዚህም ርካሽ ተወዳጅነትን ለማትረፍ የአገርን ሠላምና ደህንነት አሳልፎ መስጠቱን የሚያሳይ ነው፡፡

ወደ ኋላ ታሪክን ተመልሶ መቃኘቱ የግለሰቡን ባዶና እርቃን አስተሳሰቦችን ለማሳየት ይረዳል፡፡ የውንጀላውንም ፍሬ ቢስነት ያጋልጣል፡፡ ለተመስገን ይህን ፅሁፍ የሰጠው ግለሰብ ፀረ ፅዮናዊ (እሥራኤል) አቋምና እስላማዊ አክራሪነትን የሚያራምድ፤ የአሸባሪነት እርምጃቸው ሁሉ ከመገፋት፣ ከበደልና ከግፍ የተነሳ የመጣ ነው ብሎ አንባቢን ለማሳመን የሚደረግ መንደርደር መሆኑንም ልብ ይሏል፡፡

ተመስገን ደሣለኝ ብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት የአንድ አገር መሠረታዊ ምስሶዎችና ማገሮች፤ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዎች መሠረታዊ ምርኩዞች መሆናቸውን ቢያውቅም አያውቅም፡፡ የእሱና የመሰሎቹ ዓላማ አሸባሪውን፣ አክራሪውን፣ ፅንፈኛ ተቃዋሚውንም በጋራ አሰባስበው አስተባብረውና አስተቃቅፈው፤ ኢሕአዴግ ላይ ባላቸው የከረረ ጥላቻ በእርዳ ተራዳ ተነስተው፤ አገራቱን ጭራሽ እንዳልነበረች አድርገው ለመበታተን የደም መፋሰስ ማዕከል፤ የተለያዩ አሸባሪዎች መፈንጪያ፤ የእርስ በእርስ የጦርነት አውድማ ለማድረግ ነው፡፡

ፕሮፎሰር መሥፍንም አመፅ አይመጣም ብሎ የሚያስብ ጅላጅል ቂል ነው ሲል በቅርቡ ፅፈዋል፡፡ እንዲያውም አማራው የታል?  የለም ያልኩት ትክክል ነው፤ ቢኖር ኖሮ በደል ሲበዛበት ይነሳ ነበር የሚል ዘረኛ የሆነ የአትነሱም ወይ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ከእነሱ የቀደሙ አባቶች በሕብረትና በመቻቻል ጠብቀዋት የኖሩትን አገር ለመበታተን፤ እንድትጠፋ የሽብርና የአሸባሪዎች መናኸሪያ ሆና በየቦታው እንድትቦጫጨቅ፤ ግፍ በዛ በደል በዛ ተነስ በሚል ጩኸት ወጣቱን በጥላቻ እየመረዙና እየነተነቱ እንዲተላለቅ እያስተማሩ አዘጋጅተውታል፡፡ አስገራሚው ነገር ከዚህ ሁሉ በኋላ ኢትዮጵያ እንደ አገር ትቀጥላለች ወይንስ የጅብና የአውሬ መፈንጪያ ትሆናለች? የሚለው አስፈሪ ግምት ነው፡፡

ተመስገንም ፕሮፌሰር መሥፍንም የያዙት አገርም፣ ሕዝብም እኛም እንጥፋ የሚል ነው፤ ይህንን እጅግ አረመኔያዊና በሥልጣን እራሮት የተመላ ስካርና እብደት ሕዝብ አይሰማም አይቀበላቸውም፡፡ ወደ ዋናው የአልሸባብ ጉዳይ "የሽብር ዘ ፍጥረት" ስንመለስ የተመስገን ደሣለኝ ሐተታዎች ተራና መናኛ መሠረትም የሌላቸው ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

መለስ የኢትዮጵያ ጦር ሶማሊያ ይግባ የሚለውን ሀሳብ በፓርላማ ያስፀደቀው የዛሬ አሥር ዓመት ነው፤ ሶማሊያ በኢትዮጵያ ላይ በግብፅ እየተረዳች ኦጋዴንን ይገባኛል ግዛቴ ነው በሚል መነሻ የሶማሊያ ሰርጎ ገቦች በነሽርማርኬም ሆነ በጄኔራል ዚያድ ባሬ ዘመን አንድም ቀን ለኢትዮጵያ ተኝተው አያውቁም፡፡

በጃንሆይ ዘመን በተደጋጋሚ በኦጋዴን በኩል የሚቃጣው የሶማሊያ ሰርጎ ገቦች ጥቃትና የአካባቢው ነዋሪ ተባባሪነት በወቅቱ የቀጠናው የኢትዮጵያ ጦር አዘዥ የነበሩትን ጄኔራል አማን አምዶምን ከትዕዛዝ ውጭ ድንበር ጥሰው ወደ ሞቃዲሾ ለመገስገስ ያበቃቸው ሲሆን የተመለሱት በንጉሱ ቁጣና ትዕዛዝ ነበር፡፡ የግብፁ የቀድሞ መሪ ኮሎኔል ጀማል አብደል ናስር እስላማዊውን ፓርቲ ጀብሀን በኤርትራ እንዲቋቋም ሲመሰርትና ሲረዳ በሌላ ጐኑ ሶማሊያን እያስታጠቀ የኦጋዴንን መገንጠል ያበረታታ ነበር፡፡

በደርግ ዘመን የንጉሱን ከሥልጣን መውረድ ተከትሎ አሁን ነው ኢትዮጵያን መውረር ያለብን በሚል ጄኔራል ዚያድ ባሬ ሲወስንና በ1969 ዓ.ም በከፍተኛ ሜካናይዝድ፤ እግረኛ ክፍለ ጦሮች፣ የመድፍና ቢኤም ሻለቆች በልዩ ሁኔታ በተደራጁ ታንከኛና የኮማንዶ ክፍለ ጦሮች በመታገዝ ምንም ዘመናዊ መሣሪያና በቂ ሠራዊት ያልነበራትን የኢትዮጵያ ድንበር 700 ኪ.ሜ ጥሶ ሲገባ ግዛቴም እስከ

አዋሽ ድረስ ነው ብሎ ሲያውጅ ሙሉ ወታደራዊ ትጥቁ የተሸፈነው በግብጽ መንግሥት ነው፡፡

በዚያን ወቅት ቀደም ሲል ንጉሱ በሥልጣን ላይ እያሉ ከአሜሪካን መንግሥት ገንዘብ ከፍለው የገዙትና ወደ ኢትዮጵያ ያልገባ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ እንዲሰጠው ደርግ ሲጠይቅ የአሜሪካው የጂሚ ካርተር መንግሥት ከልክሏል፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ እንድትወረር አሜሪካን ፈቅዳለች፡፡ ሩሲያ (ሶቪየት ሕብረት) ዘመናዊ መሣሪያ በብድር ገንዘብ ስትሰጥ የመንና በተለይ ኩባ ተዋጊ ሠራዊት አሰልፋ ለኢትዮጵያ ታላቅ መስዋዕትነትን ከፍላለች፡፡

የኢትዮጵያ መደበኛ ሠራዊት ሦስት መቶ ሺህ የሚሊሺያ ሠራዊት አሰልጥኖ በመምራት ታላቅ መስዋዕትነት ተከፍሎ የሶማሊያን ወራሪ ጦር ጠራርጎ ከግዛቱ አስወጥቷል፡፡ በጣም በርካታ ሕዝብ አልቋል፤ ንብረት ውድሟል፡፡ ሶማሊያ በግብፅና በፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች የማይሸር የጠላትነት ስሜት በመረዳቱ ደርግ ሶማሊያን በማፈራረስና በመበታተን ረገድ ቁልፉን ሚና ተጫውቷል፡፡

ሶማሊያ መንግሥት አልባ የሆነችው በጦር አለቆች በየጐጡ መመራትና በእርስ በእርስ ውጊያ መታመስ በጀመረችበት ወቅት ነው፡፡ በአዲስ መልክ የተደራጀው ዓለም አቀፉ እስማዊ አክራሪ ኃይል (ጅሀዲስት) ከአፍጋኒስታን በመነሳት ሶማሊያን መሸሸጊያ ገነቱ ያደረጋት፤ ቢንላደን ከታሊባን ተዋጊዎች ይዞ ሶማሊያ በመግባት 17 የአሸባሪዎች ማሰልጠኛ ጣቢያ አቋቁሟል፡፡ የተለያዩ አገራት ዜግነት ያላቸው የአልቃይዳ አሸባሪ ቡድን አባላት ሶማሊያን እንደ ልብ ፈንጭተውባታል፡፡ አልኢትሀድ አል ኢስላሚያ በሶማሊያ መሬት የተመሰረተው በዚያን ወቅት ነበር፡፡ ኢላማውም ኢትዮጵያ ነበረች፡፡

የሶማሊያን ግዛት በማለፍ የኢትዮጵያን ድንበር በመጣስና ወደ ግዛታችን ዘልቆ በመግባት መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡ ቢንላደን በሶማሊየ 17 ቦታዎች የከፈተው የጅሀድ ተዋጊዎች ሥልጠና በዋናው ዓለም አቀፍ አሸባሪ አልቃይዳ የሚመራ ነው፤ ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ፣ ኬንያ፣ ኡጋንዳና ታንዛንያ የቅርብ ኢላማዎቹ ናቸው፡፡ በረዥሙ መላው አፍሪካና አውሮፖን ያማተረ ነበር፡፡

የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር እንደ አንድ ታጣቂና ነፍጥ ያነገበ እስላማዊ ቡድን በሶማሊያ ከሚገኙት የጅሀድ ድርጅቶችና የጐሣ አለቆች ጋር ከአል ኢትሀድና አል ኢስላሚያ ቀጥሎ ከተፈጠረው በዳሂር አዌይስ ሊቀመንበርነት ይመራ ከነበረው በአደባባይ ኦጋዴን የሶማሊያ ግዛት ስለሆነች እናስመልሳለን ይል የነበረው እስላማዊ ሕብረት ከተዳከመም በኋላ በሥፍራው ከተተካው የወጣት ጅሀዳዊ ኃይል ከሆነው አልሸባብ ጋር በቅንጅትና በሕብረት ኢትዮጵያ ላይ ዘምተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ሰርጐ የገባውን የአልኢትሀድ አል ኢስላሚያ ኃይል ሙሉ በሙሉ ሲመታ የተገኙት የተለያዩ አገራት ዜግነት የነበራቸው አክራሪ ሙስሊም የአሸባሪ ድርጅቱ አባላት ነበሩ፡፡ ከእነዚህም ሆነ ሶማሊያ ከሚገኙት ሌሎች የጅሀድ ዓለም አቀፍ አሸባሪ ኃይሎች ጋር በቅርበት የሚሰራው ኦብነግ በራሱ የኦጋዴን ሕዝብ ውስጥ በመመሸግና ተቀላቅሎ በመኖር የስለላ ሥራዎችን እየሰራ ለራሱ ወታደራዊ ክንፍ እያቀበለ የኢትዮጵያን ሠራዊት ሲወጋ ቆይታል፡፡

የኢትዮጵያን የመከላከያ ኃይል በደፈጣ ውጊያና ፈንጂ በመቅበር፣ ተመልሶም ሕዝቡ ውስጥ በመቀላቀል ለመለየት እስከሚያስቸግር ድረስ ኦብነግ ከባድ ፈተናዎችን ደቅኖ ነበር፡፡ ኦብነግ በሶማሊያ ከሚገኙት የጅሀድ ኃይሎች ከኤርትራና ከግብፅም ጭምር በወታደራዊ ሥልጠና በትጥቅ በመረጃና በሚዲያ ሽፋን ይረዳ ነበር፣ በዚያው አካባቢም የኦነግ ታጣቂ ኃይል በተለይም እስላማዊ ክንፉ በተመሳሳይ ከተጠቀሱት አካሎች እየተረዳና እየታገዘ በምሥራቅ ኢትዮጵያና አልፎም አዲስ አበባ የዘለቀ የፈንጂ ጥቃት ለማድረስ ተንቀሳቃሷል፡፡

ይህንን አደገኛና በአሸባሪዎች የሚደገፍ ኃይል ተከታትሎ ለመምታት እንዲሁም ምሽግ አድርጐ ከሚጠቀምበት ሕዝብ ውስጥ ነጥሎ ለማውጣት የኢትዮጵያ ሠራዊት ባደረጋቸው ረዥምና ተከታታይ ውጊያዎች በንብረትም የሰው ሕይወትም ላይ አደጋ ደርሷል፡፡ በአካባቢው በእርዳታ ስም ይንቀሳቀሱ የነበሩ ዓለም አቀፍ የስብዓዊ እርዳታ ድርጅቶች የነዚሁ ወገኖች ተባባሪና አጋዥ፣ መረጃ አቀባይ ሆነው በመገኘታቸው ነው እንዲወጡ የተደረገው፡፡ ይህ ደግሞ አንድ ሉዓላዊ መንግሥት ለብሔራዊ ደህንነትና የሕዝብን ሠላም ለማስከበር ሲል የሚወስደው እርምጃ ነው፡፡

ማዕከላዊ መንግሥት በሌላትና የዓለም አቀፍ እስላም አክራሪዎች የአልቃይዳና የእነ አልሸባብ መፈንጨ ያ በሆነችው ሶማሊያ እያደገና እየተንሰራፋ የመጣው አደጋ ከማንም በላይ ታላቅ ጉዳትና ጥፋት የሚያደርሰው ጎረቤት በሆነችው ኢትዮጵያ ላይ ነው፡፡ ከእስላማዊ ሕብረት መዳከምና መፍረስ  በኋላ በእግሩ የተተካው በሶማሊያ አክራሪ ሙስሊሞች የተሞላው አልሸባብ (የወጣት ክንፍ) በአስገራሚ ፍጥነት አብዛኛውን የሶማሊያ ግዛት ተቆጣጥሮ በሽሪአ የሚመራ እስላማዊ መንግሥት ሲያቋቁም፤ የአልቃይዳ ክንፍ ሆኖ አካባቢውን ሲቆጣጠር አሁንም ቀጣዩ ኢላማቸው ኢትዮጵያ መሆኗ ለውይይትም ለክርክርም አይቀርብም፡፡

ይህ ሁኔታ በእጅጉ ያሳሰበው የአፍሪካ ሕብረት፣ የአውሮፖ ሕብረት፣ አሜሪካና ሌሎችም  ወደ ዓለም አቀፍ አደጋነት የሚለወጥ የአሸባሪነት አደጋ ለመቅጨት ብዙ አውጠንጥነዋል፡፡ እነሱ ከሶማሊያ በብዙ ሺህ ማይልስ ርቀት የሚገኙ ሲሆን ቅርቡና ግዙፉ አደጋ በኢትዮጵያ ላይ መሆኑ ስለሚታወቅ ኢትዮጵያ ሠራዊቷን ወደ ሶማሊያ አስገብታ አልሸባብን እንድትመታ ጥያቄ ሲቀርብላት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር በፖርላማ አቅርበው ሠራዊቱ እንዲገባ አፀደቁ፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊትም በሶማሊያ ምድር ገብቶ ከባድ ጦርነቶችን በመግጠም የአልሸባብን ሰፊ ይዞታዎች አስለቀቀ፤ መስዋዕትነት ተከፈለ፡፡ ወደ ሶማሊያ መሬት ዘልቆ የተገባው አደጋው ወደ ኢትዮጵያ ግዛትና መሬት እንዳይገባ እዚያው ለማምከን እንጂ የአሜሪካንን ጥቅም ለማስከበር አይደለም፡፡ የሶማሌያ ጎረቤት እኛ እንጂ አሜሪካን አይደለችም፡፡

አልሸባብ በኢትዮጵያ ሠራዊት በተደጋጋሚ ተመትቶ ውድቀት ስለደረሰበት በኢትዮጵያ ላይ እስከዛሬ አምስት ጊዜ ያህል የጅሀድ ጦርነት አውጇል፡፡ ወታደራዊ ሥልቱን ከፊት ለፊት ውጊያ ወደ ሽምቅ ውጊያ በመለወጥ በአነስተኛ የሰው ኃይል ከባድ ጥፋት የማድረስ፤ አጥፍቶ ጠፊዎችን የማሰማራት፤ ሕዝብ በሚገኝባቸው ቦታዎች ላይ አደጋ በመጣል በፈንጂና ቦምብ መምታት ያገኘውን ሰው ወደ ማጥፋት ተሸጋግሯል፡፡

የኢትዮጵያ ሠራዊት ከሶማሊያ ለቆ ከወጣ በኋላ እንደገና አልሸባብ በከፍተኛ ፍጥነት በመንሰራፋቱና የውጊያ አቅሙ በማደጉ የአፍሪካ ሕብረት የኡጋንዳንና የኬንያን ሠራዊት ቢያሰማራም ለውጥ ስላልመጣ አሁንም ኢትዮጵያ ሠራዊቷን

እንድታስገባ ተጠይቃ በመላክ በከባድ ውጊያ በርካታ ቦታዎችን ከአልሸባብ አስለቅቃለች፡፡

በሶማሊያም መንግሥት ተመስርቶ አንፃራዊ ሠላም ሰፍኖ ዓለም አቀፍ ኤምባሲዎች ተከፍተዋል፡፡ የአሜሪካ እንግሊዝ ቻይናና ሌሎችም፡፡ የኬንያ ሠራዊት ሶማሊያ በመግባቱና በመዋጋቱ በኬንያ ላይ ጅሀድ ያወጀው አልሸባብ ተሳክቶለት አውሮፓውያን በሚገለገሉበት የገበያ ማዕከል በሌሎችም ቦታዎች ተደጋጋሚ አደጋ በኬንያ አድርሷል፡፡ ዒላማዎቹ የመንግሥትና የሕዝብ ተቋማት፤ አየር ማረፊያዎች፤ ታላላቅ የገበያ ማዕከሎች፤ የሕዝብ ትራንስፖርት መገልገያዎች፤ የምዕራባውያን ኤምባሲዎች፤ የመዝናኛ ሥፍራዎችና ሌሎችም ናቸው፡፡ ይህን የሚፈጽመው በየአገራቱ በመለመላቸው አክራሪ አሸባሪዎች የመረጃ ትብብርና ጥናት እንዲሁም ተሳታፊነት እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ተመስገን ደሣለኝ በሽብር ዘፍጥረት ፅሁፉ ኢትዮጵያ አልሻብብን ለመዋጋት ወደ ሶማሊያ ምድር ሠራዊቱን ያዘመተችው የአሜሪካንን ጥቅም ለማስከበር እንጂ ለራሷ ስትል አይደለም በማለት በሶማሊያ ጦርነት ተሳታፊ ነበሩ የሚላቸውን የኢትዮጵያ ሠራዊት አባላት አስተያየት በሥውር ስም በማድረግ ገልጿል፡፡ በውጊያው ላይ የአሜሪካን ጄቶች ታይቶ በማይታወቅ መሣሪያ ሲደበድቡ አይተን የማናውቀው በመሆኑ አንገታችንን ቀብረን ደንግጠናል ማለታቸውን አስነብቧል፡፡ አሜሪካ ባላት የቴክኖሎጂና ወታደራዊ የበላይነት በሣተላይት ከምታገኘው የአልሸባብ ሠራዊት ይዞታ፤ ንቅናቄ መሣሪያና ድርጅት ላይ ፈጥና እርምጃ በመውሰድ ኃይሉንና አቅሙን መስበሯ በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ሊያደርስ የሚችለውን አደጋ ይቀንሳል እንጂ ሌላ ችግር የለውም፡፡ አክራሪው እስላማዊ አሸባሪ ኃይል አልሸባብ በአካባቢው አገራት ላይ አደጋ ለማድረስ ከመሞከር መቼም አይተኛም፡፡ በኢትዮጵያ ላይ የተጋረጠ የተደቀነ ታላቅ አደጋ ነው፡፡

በሶማሊያ በኩል ቀድሞ በድንበር በኋላም በእስላማዊ አክራሪና አሸባሪ ኃይሎች አቀናባሪነት በኢትዮጵያ ላይ ያንዣበበውን አደጋ ለመቀልበስ የኢትዮጵያ ሠራዊት አህጉራዊና አለም አቀፍ ጥሪዎችን ተቀብሎ በሶማሊያ በመግባት የወሰደው እርምጃ ተገቢና ትክክል ነው፡፡ እኛ ድንበራችንን አልፈን ባንሄድም በእርግጠኛነት ድንበራችንን ጥሶ በመግባት በራሳችን ግዛት ውስጥ ውጊያ ሊገጥመን ይመጣ

እንደነበር መናገር ይቻላል፡፡ ስለዚህም በራሱ መሬት ላይ ሄደን መፋለማችን ወደ እኛ ይዞት ሊዘምት የነበረውን አስከፊ አደጋ በብዙ እጅ መቀነስ አስችሏል፡፡

ዛሬ አክራሪው እስላማዊ ኃይል በኢራቅና በሶሪያ መካከል ድንበር የለም፤ ሁሉም ሙስሊሞችና የሙስሊም መሬት ነው ብሎ የሙስሊም ካሊፋይት በሸሪዓ የሚመራ መንግሥት አውጇል፡፡ ለጊዜው ማንም ያገደው የለም፡፡ አሜሪካንም፣ እንግሊዝም ተደናግጠው መመልከት ይዘዋል፡፡ አይሲስ ለመካከለኛው ምሥራቅ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለምም አደጋ መሆኑ እየተነገረ ነው፡፡

ቀጣዩ ሁኔታ አይታወቅም፡፡ ኢትዮጵያም በአልሸባብና ተጓዳኝነት ባላቸው አሸባሪ ኃይሎች ላይ የወሰደችው እርምጃ በቀዳሚነት ከራሷ ብሔራዊ ጥቅም ሠላምና ደህንነት አንፃር እንጂ የሌላ ወገንን ጥቅም ለማስከበር አይደለም፡፡ ቀጣዩ የዓለም ፈተናና ጦርነት ከእነዚሁ ዓለም አቀፍ የሙስሊም አክራሪ ኃይሎች ጋር የሚደረገው የሞት የሽረት ትግል ነው፡፡ ኢትዮጵያም ራሷን በብዙ መልኩ ነቅታ ትጠብቅ ዘንድ ግድ ነው፡፡